የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት
Ethiopian Metrology Institute

# የኢትዮጵያ ስነልክ ኢንስቲትዩት
# የቴክኒክ ስራዎች አሰራር ማኑዋል

Catalog

1. ተቋማዊ መሰረት ... 1
1.1. አጠቃላይ የአሰራር ማኑዋሉ ዓላማ ... 1
1.2. የተቋሙ ህጋዊ ስልጣን ... 1
1.3. ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች ... 1
1.4. የተቋሙ ስትራቴጂክ ዓላማዎች ... 2
2. አስተዳደር እና ተቋማዊ መዋቅር ... 4
2.1. የድርጅታዊ መዋቅር ... 4
2.2. የዋና ዳይሬክተር፣ የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና የዘርፍ ኃላፊዎች ሚና። ... 5
3. አገልግሎቶች እና ተግባራት ... 9
3.1. ከአገልግሎቱ ጋር የተያያዙ አጠቃላይ መረጃዎች ... 9
3.2. በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡ የቴክኒክ አገልግሎቶች ዝርዝር መግለጫ ... 10
3.3. የአሰራር ሂደቶች፣ ደንበኞች አገልግሎቱን ለማግኘት ማለፍ ያለባቸው ቅደም ተከተሎች ... 10
3.4. የአገልግሎት ደረጃዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች ... 11
3.5. የተቋሙ ኮር የሥራ ሂደት ክንውን ... 12
4. ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች ... 22
5. ውጫዊ ግንኙነት እና አጋርነት ... 25
5.1. የኢንስቲትዩቱ ተገልጋዮች እና ባለድርሻ አካላት ... 25
6. ደንበኞች መብትና ግዴታ ሰንጠረዥ ... 31
7. የኢንስቲትዩቱ የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ ... 31
8. ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚደረጉ ትብብሮች ... 32
9. የማኅበረሰብ ተሳትፎ ተግባራት ... 33
10. ዓለም አቀፍ ወይም ቀጠናዊ አባልነቶች ... 34
11. አባልነት እና ዕውቅናዎች: ... 35
12. የመገናኛ መረጃዎች ... 36
ዋና መሥሪያ ቤት እና የቅርንጫፍ ቢሮዎች ... 36
ዋና መስሪያ ቤት ... 36
ቅርንጫፍ ቢሮዎች ... 36
13. የሥራ ክፍል ሀላፊዎች ዝርዝር መገናኛ ... 37
የኢንተርኔት መርጃዎች እና የመረጃ ቋቶች ... 37
ማኅበራዊ ሚዲያ እና የመገናኛ መስመሮች ... 37
14. አባሪዎች ... 38
አባሪ 1፡- የኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት የደንበኞች ቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስነ-ስርዓት ... 38
አባሪ 2፡ የኢንስቲትዩቱ ስነምግባር መርሆዎች ... 40
አባሪ 3፡ የካሊብሬሽን ስራዎች ብቃት ... 42

# 1. ተቋማዊ መሰረት

## 1.1. አጠቃላይ የአሰራር ማኑዋሉ ዓላማ

የኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት በሀገሪቱ የጥራት መሰረተ-ልማት ግንባታ ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና ያለው ብሄራዊ ተቋም ነው። ይህ የአሰራር መመሪያ ተቋሙ የሀገሪቱን የልኬት ስርዓት ለማዘመን፣ የኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ እና የህዝቡን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚከናውናቸውን ሁለንተናዊ ተግባራት በዝርዝር የሚያሳይ ሰነድ ነው።

ኢንስቲትዩቱም የሀገሪቱን የልኬት መሰረት ከዓለም አቀፍ የአሃዶች ስርዓት (SI) ጋር በማስተሳሰር እና ብሔራዊ ኢታሎኖችን በአስተማማኝ ሁኔታ በመጠበቅ የልኬት ስርዓቱን የማዘመን ስራ ይከውናል። ከዚህም ጎን ለጎን ለአገልግሎት ሰጪዎች እና ለአምራች ድርጅቶች ስልጠናና የምክር አገልግሎት በመስጠት የቴክኒክ ብቃታቸውን የሚያጎለብት ሲሆን፣ በሳይንስ መሳሪያዎች አመራረጥ፣ ግዥ እና ጥገና ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በቴክኒክ ድጋፍ ይሞላል። ተቋሙ ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ መድረኮች በመወከልና የልኬት ውጤት ንፅፅር በማድረግም፣ የሀገሪቱ የልኬት አገልግሎት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትና ተወዳዳሪነት እንዲኖረው በትኩረት የሚሰራ ተቋም ነው።

በአጠቃላይ ይህ ማኑዋል ኢንስቲትዩቱ እንደ ሀገር የተጣለበትን ህጋዊና ሙያዊ ኃላፊነት ለመወጣት የሚያከናውናቸውን ተግባራት፣ ለአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች በዝርዝር የሚያስረዳ ሰነድ ነው።

## 1.2. የተቋሙ ህጋዊ ስልጣን

የኢትዮጵያ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 555/2016 የተቋቋመ እና ተጠሪነቱ ለንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሆነ ብሔራዊ ተቋም ነው። ኢንስቲትዩቱ በዋናነት የመለኪያ መሣሪያዎችን ካሊብሬሽን የማከናወን፣ የሕክምና፣ የአናላይቲካልና የሳይንስ መሣሪያዎችን የመጠገን፣ እንዲሁም በዘርፉ አቅም የሚገነቡ ስልጠናዎችንና የማማከር አገልግሎቶችን የመስጠት ሰፊ ተልዕኮ ተሰጥቶታል። በተጨማሪም የዘርፉን ችግሮች የሚፈቱ የምርምር ሥራዎችን በማከናወን የሀገሪቱን የጥራት መሠረተ-ልማት የማዘመን ሚና ይጫወታል።

## 1.3. ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች

**ተልዕኮ**

በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች የጎለበተ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት፣ ችግር ፈቺ ምርምሮችን በማከናወን፣ ቀጣይነት ያለው አቅም በመገንባትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማምጣት ለደንበኞቻችን ብቃት ያለው አገልግሎት በመስጠት የምርትና የአገልግሎት ጥራትና ውጤታማነትን የማሳደግ ሚናውን በመወጣት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት መደገፍ

**ራዕይ**

በ2022 ዓ.ም በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሣሪያዎች ዘርፍ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው በአፍሪካ ተመራጭ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት መሆን

**ዕሴቶች**

- መሰጠት
- ማቀናጀት
- መላቅ

በዚህም ኢንስቲትዩቱ ለትክክለኛ ልኬት፣ ለፍትሐዊ ንግድና ለላቀ ጥራት የሚሰራ ሲሆን ትኩረቱም

- ✓ ማንኛውም የልኬት ውጤት በሳይንሳዊ መረጃና በማስረጃ ላይ ብቻ የተመሠረተ ማድረግ፣
- ✓ ዓለም አቀፋዊ ትስስርን በማስጠበቅ አለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ፣
- ✓ የጥራት መሠረተ ልማት ስርዓትን መደገፍ፣

## 1.4. የተቋሙ ስትራቴጂክ ዓላማዎች

ኢንስቲትዩቱ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ውስጥ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምርን በማስፋፋት፣ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ትብብሮችን በማጠናከር፣ እንዲሁም የልኬት ትክክለኝነትንና የዕርከን ተዋረድ ትስስርን በላቀ ደረጃ በማረጋገጥ የሀገሪቱን የሥነልክ መሰረት ለማዘመን አልሟል። በእነዚህ ስትራቴጂካዊ ጥረቶች አማካኝነትም፣ የተቋሙ አገልግሎቶች ሙሉ ዓለም አቀፍ ዕውቅናና ተቀባይነት እንዲኖራቸው በማድረግ የኢትዮጵያን የንግድና የኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነት የማሳደግ ግብ ይዞ እየሰራ ይገኛል።

**ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማካሄድ**

- በሳይንስ መሳሪያዎች እና በሥነ-ልክ ዘርፍ ሳይንሳዊ ምርምርና ጥናት ለማከናወን የሚያስችሉ ተቋማዊ የመሰረተ ልማት ግንባታ ተግባራትን ማከናወን ።
- የአምራችና አገልግሎት ሰጪ ኢንዱስትሪዎችን ችግር የሚፈቱ፣ ለአካባቢ ጥበቃና ለህብረተሰብ ጤና እንክብካቤ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማካሄድ፣
- በሀገር ውስጥ ገበያ የማይገኙ የሳይንስ መሳሪያዎች አካላት በምህንድስና አግባብ ተዘጋጅተው ለጥገና፣ ለሥልጠናና ለትምህርት ግብዓት እንዲውሉ በማድረግ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳለጥ ፣

**ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ትብብር ተሳትፎን ማጠናከር**

- ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር ቅንጅት በመፍጠር የሀገሪቱን ፍላጎት የሚያሟላና ጠንካራ ብሔራዊ የሥነ-ልክ ሥርዓት መዘርጋት፣

- በዓለም አቀፍ የሚዛንና መስፈሪያ ጠቅላላ ጉባኤ (CIPM MRA) እና በአፍሪካ ሜትሮሎጂ (AFRIMET) ቴክኒካዊ ስብሰባዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣
- ኢንስቲትዩቱ የዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት (BIPM) ሙሉ አባል በመሆን የሀገሪቱን ጥቅም ማስከበር፣

## የልኬት ትክክለኝነትና የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማስጠበቅ

- ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ ስታንዳርዶች ዓለም አቀፍ ተቀባይነት እንዲኖራቸው የላቦራቶሪ ሥርዓት በመዘርጋት የትክክለኝነት መጠናቸውና ትስስራቸው ተጠብቆ እንዲቆይ ማድረግ፣
- በሀገር ውስጥ ያሉ የካሊብሬሽን ላቦራቶሪዎች ብሔራዊ የዕርከን ተዋረድ ትስስር እንዲጠበቅና በአቻ ላቦራቶሪዎች ግምገማ ተቀባይነት እንዲያገኙ መስራት፣
- የብሔራዊ መለኪያ ስታንዳርዱ በአገሪቱ ውስጥ የመጨረሻው ትክክለኛ የልኬት መጠን ሆኖ ማገልገሉ ይረጋገጣል ።

## ዓለም አቀፍ ዕውቅናና ተቀባይነት ማጠናከር

- የኢንስቲትዩቱ የልኬት ብቃት በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ዳታ ቤዝ (KCDB) ላይ እንዲሰፍር በማድረግ የካሊብሬሽን ሰርተፍኬቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ይደረጋል ።
- በዓለም አቀፍና አህጉራዊ የእርስ በርስ የላቦራቶሪ ንፅፅር ፕሮግራሞች ላይ በመሳተፍ የልኬት ብቃት ይረጋገጣል ።

# 2. አስተዳደር እና ተቋማዊ መዋቅር

## 2.1. የድርጅታዊ መዋቅር



## 2.2. የዋና ዳይሬክተር፣ የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና የዘርፍ ኃላፊዎች ሚና።

**የዋና ዳይሬክተሩ ዋና ዋና ተግባራትና ኃላፊነቶች**

### i. ስትራቴጂካዊ አመራር መስጠት

- የኢንስቲትዩቱን አጭር፣ መካከለኛና የረጅም ጊዜ ስትራቴጂካዊ ዕቅዶች ማጽደቅና አፈጻጸማቸውን መከታተል።
- ተቋሙ በደንብ ቁጥር 555/2016 የተሰጠውን ተልዕኮ (ካሊብሬሽን፣ ጥገና፣ ስልጠናና ምርምር) በአግባቡ መወጣቱን ማረጋገጥ።

### ii. ዓለም አቀፍና አገራዊ ግንኙነቶችን መምራት

- ኢንስቲትዩቱን በዓለም አቀፍ የልኬት ድርጅቶች (ለምሳሌ BIPM, AFRIMETS) እና በአገራዊ መድረኮች መወከልና የሀገሪቱን ጥቅም ማስከበር።
- ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነት መፍጠር።

### iii. የሀብትና የፋይናንስ አስተዳደር

- የተቋሙን ዓመታዊ በጀት ማዘጋጀትና ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ማስጸደቅ፣ በጀቱም ለታለመለት ዓላማ መዋሉን መቆጣጠር።
- ለላቦራቶሪዎችና ለምርምር ሥራዎች የሚያስፈልጉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችና ግብዓቶች እንዲሟሉ መምራት።

### iv. የጥራትና የቴክኒክ የበላይነትን ማረጋገጥ

- የኢንስቲትዩቱ የካሊብሬሽንና የጥገና አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ (እንደ ISO/IEC 17025 ያሉ) መሆናቸውን ማረጋገጥ።
- በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡ የምስክር ወረቀቶችና የቴክኒክ ውሳኔዎች ተዓማኒነት እንዲኖራቸው የበላይ ክትትል ማድረግ።

### v. የሰው ኃይል ልማትና አስተዳደር

- ብቁና የሰለጠኑ የሜትሮሎጂ ባለሙያዎች፣ የጥገና ኢንጂነሮችና ተመራማሪዎች እንዲፈሩ ምቹ የሥራ አካባቢ መፍጠር።
- የተቋሙን መዋቅርና የአሠራር ሥርዓቶች በየጊዜው በማሻሻል የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ ማድረግ።

### vi. ምርምርና ፈጠራን ማበረታታት

- በዘርፉ ያሉ የቴክኒክ ችግሮችን የሚፈቱ የምርምር ሥራዎች እንዲከናወኑና የፈጠራ ሥራዎች እንዲበረታቱ ድጋፍ መስጠት።

## የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ዋና ዋና ተግባራትና ኃላፊነቶች

### i. የቴክኒክ አገልግሎቶችን በበላይነት መምራት

- የካሊብሬሽን፣ የጥገና፣ የማማከርና የስልጠና አገልግሎቶች በተቀመጠላቸው የጥራት ደረጃና የጊዜ ሰሌዳ መከናወናቸውን ማረጋገጥ።
- በላቦራቶሪዎች የሚሰጡ የልኬት ውጤቶችና የጥገና ሥራዎች ትክክለኛነትና ተዓማኒነት ላይ የበላይ ክትትል ማድረግ።

### ii. የላቦራቶሪዎች ብቃትና እውቅና

- የኢንስቲትዩቱ ላቦራቶሪዎች ዓለም አቀፍ የ ISO/IEC 17025 ዕውቅና እንዲያገኙና የነበረውንም እንዲያስጠብቁ የቴክኒክ አመራር መስጠት።
- የልኬት መሣሪያዎች ከዓለም አቀፍ ስታንዳርዶች ጋር ያላቸው ትስስር (Traceability) የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ።

### iii. የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ

- ደንበኞች መሣሪያዎቻቸውን ለካሊብሬሽንና ለጥገና ሲያመጡ የሚስተናገዱበትን ሂደት ይበልጥ ቀልጣፋና ዲጂታላይዝድ እንዲሆን መምራት።
- የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱን የሚያሳጥሩና ጥራቱን የሚጨምሩ አዳዲስ አሠራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን በሥራ ላይ ማዋል።

### iv. የሰው ኃይል ቴክኒካዊ አቅም ግንባታ

- በስነ-ልክ እና በሳይንስ መሣሪያዎች ጥገና ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎችና ኢንጂነሮች ወቅታዊና ከፍተኛ ደረጃ ያለው ስልጠና እንዲያገኙ ማመቻቸት።
- የባለሙያዎችን የሥራ አፈጻጸምና የቴክኒክ ብቃት በየጊዜው መገምገም።

### v. የምርምርና ልማት ሥራዎችን ማስተናገድ

- በዘርፉ ያሉ የቴክኒክ ችግሮችን የሚፈቱ ምርምሮች በላቦራቶሪዎችና በምርምር ክፍሎች ውስጥ እንዲከናወኑ ማበረታታትና መደገፍ።
- አዳዲስ የልኬት ዘዴዎችና የጥገና ስልቶች ተጠንተው ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ።

### vi. የደንበኞች እርካታና ቅሬታ አያያዝ

- ደንበኞች በቴክኒክ አገልግሎቱ ላይ ያላቸውን እርካታ መከታተልና ለሚቀርቡ ውስብስብ ቴክኒካዊ ቅሬታዎች መፍትሔ መስጠት።

## የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ

ተጠሪነቱ ለኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ሆኖ፡-

- የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ጉዳዮችን፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስራዎችን፣ የግዢና ፋይናንስ አስተዳደርን፣ የብቃትና ሰው ሀብት አስተዳደር፣ የሰቶችና ማህበራዊ ጉዳይ አካትቶ ትግበራ ስራዎችን እንዲሁም የመሰረታዊ አገልግሎት የማቀድ፣ የማደራጀት፣ የመምራትና ማስተባበር፣
- የኢንስቲትዩቱን ተልዕኮ ለማሳካት ስራቴጂያዊ ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት ያለው ሲሆን በስሩ ስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ፣ ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሥራ አስፈጻሚ፣ የግዥና ፋይናንስ ሥራ አስፈጻሚ፣ የብቃትና ሰው ሀብት አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ፣ ሰቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች አካትቶ ትግበራ ሥራ አስፈጻሚ፣ የመሠረታዊ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ እና ኤግዚኩዩቲቭ ሴክሬታሪ I አካቶት ይሰራል።

## የስነልክ ምርምርና ቴክኒካል ስራዎች ስራ አስፈፃሚዎች የስራ መዘርዝር

i. የዘርፉን የሥነ-ልክ ምርምር ሥራዎችን ማቀድ፣ ማደራጀትና መምራት

- የሥነ-ልክ ምርምር ሥራዎችን በበላይነት ያቅዳል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል ።
- ለምርምር አስፈላጊ የሆኑ የሰው ኃይል፣ የላቦራቶሪ መሣሪያዎችና ግብዓቶች እንዲሟሉ ያደርጋል ።
- የስትራቴጂክና ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል ።
- የላቦራቶሪዎችን ደህንነትና የመሣሪያዎችን ብቃት ለመጠበቅ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል ።

ii. የዘርፉን የሥነ-ልክ ስትራቴጂካዊ ምርምሮችን መምራትና ማከናወን

- ሀገራዊ ችግር ፈቺና የውጭ ቴክኖሎጂን የሚተኩ ስትራቴጂካዊ ምርምሮችን ያመነጫል፣ ያካሂዳል ።
- ሳይንሳዊ የምርምር ውጤቶች በታወቁ ጆርናሎች እንዲታተሙና የአእምሯዊ ንብረት መብት እንዲያገኙ ያደርጋል ።
- ከኢንዱስትሪና ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመቀናጀት የጋራ ምርምሮችን ይመራል፣ ለአማካሪነትም ያገለግላል ።
- የምርምር ውጤቶች ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ለኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነት እንዲውሉ መድረኮችን ያመቻቻል ።

iii. አገራዊ የአለካክ ሥርዓት መዘርጋትና ብቃቱን ማሳደግ

- የሥነ-ልክ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን ያመነጫል፣ ብሔራዊ ኢታሎኖች እንዲወሰኑና እንዲጠበቁ ያደርጋል ።
- የላቦራቶሪዎች የጥራት አስተዳደር ሥርዓት ዓለም አቀፍ ዕውቅና እንዲያገኝና እንዲቀጥል ይመራል ።
- በዓለም አቀፍ የርስበርስ ንፅፅር እና በቴክኒካል ኮሚቴዎች ላይ በመሳተፍ የሀገርን ጥቅም ያስጠብቃል ።
- በሳይንሳዊ፣ ኢንዱስትሪያዊና ሕጋዊ ሥነ-ልክ መካከል ውጤታማ ቅንጅት እንዲኖር ይሰራል ።

iv. በስነ-ልክ ዘርፍ አገራዊ አቅም በቀጣይነት መገንባት

- የዘርፉን የምርምር አቅም ክፍተት በጥናት በመለየት የአቅም ግንባታ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ ይተገብራል ፡፡
- የተመራማሪዎችን ዕውቀትና ክህሎት ለማሳደግ ስልጠናዎችን፣ የልምድ ልውውጦችንና ሳይንሳዊ ጉብኝቶችን ያመቻቻል ፡፡
- ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር የትምህርት ካሪኩለም ያዘጋጃል፣ የድህረ-ምረቃ ኮርሶችንም ይሰጣል ፡፡
- ለላቦራቶሪዎች ግንባታና ለቴክኖሎጂ አመላመድ የሚያስፈልጉ ቴክኒካዊ መመሪያዎችን ያዘጋጃል ፡፡

**በሳይንስ መሳሪያዎች ምርምርና ቴክኒካል ስራዎች ስራ አስፈፃሚዎች የስራ መዘርዝር**

## i. የሳይንስ መሣሪያዎች የምርምር ሥራዎችን ማቀድ፣ ማደራጀትና መምራት

- የሳይንስ መሣሪያዎች ምርምር ተግባራትን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል ፡፡
- ለምርምር አስፈላጊ የሆኑ የሰው ኃይል፣ የላቦራቶሪና የዎርክሾፕ ግብዓቶች እንዲሟሉና መሣሪያዎች በብቃት እንዲሠሩ ያደርጋል ፡፡
- የተቋሙን ስትራቴጂክና ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል ፡፡
- የምርምርና ስርፀት ባህል እንዲገነባ አዳዲስ አሠራሮችን ያጠናል፣ ተግባራዊም ያደርጋል ፡፡

## ii. የሳይንስ መሣሪያዎች ስትራቴጂካዊ ምርምሮችን መምራትና ማከናወን

- ሀገራዊ ችግር ፈቺ፣ ሀብት ቆጣቢና የውጭ ቴክኖሎጂን የሚተኩ የምርምር ስትራቴጂዎችን ይነድፋል ፡፡
- ሳይንሳዊ ምርምሮችን ያካሄዳል፤ የምርምር ውጤቶች በታወቁ ጆርናሎች እንዲታተሙና የአእምሯዊ ንብረት መብት እንዲያገኙ ያደርጋል ፡፡
- ከኢንዱስትሪና ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመቀናጀት የጋራ ምርምሮችን ያቅዳል፣ ይመራል፣ ለአማካሪነትም ያገለግላል ፡፡
- የምርምር ውጤቶችና ፕሮቶታይፖች ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ለሥራ ፈጠራ እንዲውሉ ያስተባብራል ፡፡

## iii. አገራዊ የሳይንስ መሣሪያዎች የሥራ አመራር ሥርዓት መዘርጋትና ብቃቱን ማሳደግ

- የሳይንስ መሣሪያዎች ሀገር አቀፍ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን ያመነጫል፣ የሥርዓት ዝርጋታውንም ይመራል ፡፡
- መሣሪያዎች ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን ጠብቀው አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል ሳይንሳዊ አሠራርና የጥራት አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል ፡፡

- አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና የምልስ ምህድስና የምርምር ዘዴዎችን በመቀመር ተደራሽ ያደርጋል ።
- የሳይንስ መሣሪያዎች የመጠቀም አቅምን ለማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ጋር የቅንጅት መድረክ ይፈጥራል ።

### iv. በሳይንስ መሣሪያዎች ዘርፍ አገራዊ አቅም በቀጣይነት መገንባት

- የምርምር አቅም ክፍተቶችን በጥናት በመለየት የአቅም ግንባታ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ ለመንግስት ያቀርባል ።
- ተመራማሪዎችና ተጠቃሚ ተቋማት መሣሪያዎችን የመትከልና የመንከባከብ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ስልጠናና ምክር ይሰጣል ።
- ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር የትምህርት ካሪኩለም ያዘጋጃል፣
- ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ተቋማት ጋር የእውቀትና የክህሎት ልውውጥ የሚያደርጉባቸውን መድረኮች ያመቻቻል ።

# 3. አገልግሎቶች እና ተግባራት

## 3.1. ከአገልግሎቱ ጋር የተያያዙ አጠቃላይ መረጃዎች

በኢንስቲትዩቱ ውስጥ የሚሰጡ አጠቃላይ የካሊብሬሽን አገልግሎቶች ከአገልግሎት አሰጣጡ አንፃር ጥቅል መረጃ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተቀምጧል።

| | |
|---|---|
| **የህግ ማዕቀፍ** | • የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት በደንብ ቁጥር 555/2016<br>• የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት የአገልግሎት ክፍያ ደንብ ****<br>• አገልግሎት ውል |
| ከተገልጋዩ የሚጠበቁ አሰፈላጊ ሰነዶች | • የአገልግሎት ጥያቄ<br>• የአገለግሎት ክፍያ ማረጋገጫ<br>• የሚሠራዉን ዕቃ ማምጣት<br>• ለመስክ ስራ ትራንስፖርት ማቅረብ |
| አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ | • በአካልና በኦንላይን |
| የማመልከቻ ደረጃዎች | • የመሳሪያዎች ዝርዝር<br>• ብዛት<br>• ሞዴል፣ ሴሪ_ቁጠር<br>• የመለካት አቅም<br>• ውስብስብነታቸው ከፍ ላሉ መሳሪያዎች ማንዋል<br>• የልኬት እርግጠኝነት ወሰን<br>• የማነጻጸሪ ነጥቦች/ወሰን<br>• በመስክ ለሚሰራ - ቦታ መግለፅ |
| **ማስታወሻ** | • አገልግሎቱ የሚፈለገው ጊዜ በስራ አካባቢ እና መሳሪያው ያለበት ሁኔታ ይወሰናል። |

## 3.2. በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡ የቴክኒክ አገልግሎቶች ዝርዝር መግለጫ

- ✓ የኤሌክትሮማግኔቲክ እና ሙቀት ሥነ-ልክ ምርምር እና ካሊብሬሽን
- ✓ የመካኒካል ሥነ-ልክ ምርምር እና ካሊብሬሽን ንዑስ
- ✓ የኬሚካል ሥነ-ልክ ካሊብሬሽን እና ምርምር ንዑስ
- ✓ የህክምና መሳሪያዎች ምርምር እና ጥገና አገልግሎት ንዑስ
- ✓ ህክምና ያልሆኑ መሳሪያዎች ምርምር እና ጥገና አገልግሎት

## 3.3. የአሰራር ሂደቶች፣ ደንበኞች አገልግሎቱን ለማግኘት ማለፍ ያለባቸው ቅደም ተከተሎች

የአገልግሎት ፍሰት

- የአገለግሎት ጥያቄ መቀበል እና መገምገም
- የተጠየቁ መሳሪያዎች በአገለግሎት ወሰን ውስጥ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- ከአገልግሎት ወሰን ውስጥ ላለሆኑ መዝገቦ ለደንበኛው ማሳወቅ
- የአገለግሎት ውል መኖሩን ማጣራት
- በውል ለሚሰጥ አገለግሎት የውል እድሳት ማስፈለጉን ማረጋገጥ
- የውል እድሳት ካስፈለገ ውል ማደስ
- በቅድመ ክፍያ ለሚሰጥ አገለግሎት ክፍያ ማሳወቅ እና ማስፈጸም
- ስራውን በመስክ ወይም በማእከል መለየት
- በማእከል ለሚሰጠው አገለግሎት መሳሪያ መረከብ
- በመስክ ለሚሰጠው አገልግሎት የመስክ ስራ ዝግጅት እና ጉዞ ማድረግ
- ካሊብሬሽን ማከናወን
- ሰርተፍኬት ማዘጋጀት እና ማፅደቅ
- ሰርተፍኬቱን እና መሳሪያዉን ለደንበኛው ማስረከብ



Figure 1: የአገለግሎት ፍሰት ንድፍ

## 3.4. የአገልግሎት ደረጃዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ጥራት፣ የጊዜ ገደብ እና ደንበኛው የሚያገኘው የመጨረሻ ውጤት።**

i. የካሊብሬሽን አገልግሎት የሚሰጠው የላቦራቶሪ ስራ አመራር ISO/IEC 17025፡2017 መሰረት ባደረገ መልኩ ነው፣
ii. የሳይንስ መሳሪያዎች አገልግሎት ደግሞ በ ISO 13485 Medical devices — Quality management systems — Requirements for regulatory purposes አግባብ አገልግሎቱ ይሰጣል፣

**አገልግሎቱ የሚፈልገው ጊዜ**

- ለማእከል አገልግሎት፡ መሳሪያው ወደ ላቦራቶሪ በመጣ 3 ቀናት
- ለመስክ አገልግሎት፡ አገልግሎቱ በሚሰጥበት ቦታ በተደረሰ 3 ቀናት

**ደንበኛው የሚያገኘው ውጤት**

- ካሊብሬት የተደረገ የመለኪያ መሳሪያ እና የካሊብሬሽን ሰርተፍኬት
- የተጠገነ መሳሪያ
- በዘርፉ የተሰጠ ስልጠና
- በዘርፉ የተሰጠ ምክር

## 3.5. የተቋሙ ኮር የሥራ ሂደት ክንውን

### የአገልግሎቶች ዝርዝር

**1፡-የልኬት እርከን ተዋረድ ትስስርና ስርጭት**

**ጥቅል አገለግሎት 1፡ የካሊብሬሽን አገለግሎት**

በኤሌክትሮ ማግኔቲክ እና ሙቀት ሥነ-ልክ መሪ ሥራ አስፈፃሚ የሚሰጡ አገልግሎቶች

| ተ.ቁ | አገልግሎት | የአገልግሎቱ ዓይነት | ዋጋ በብር) |
|---|---|---|---|
| 1 | የሙቀት መለኪያ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን አገለግሎት | የዲጂታል/ባይ-ሜታሊክ/LIG ቴርሞሜትር ካሊብሬሽን አገልግሎት መስጠት | 1,116 |
| | | የፕላቲነም ሬዚስታንስ ካሊብሬሽን | 4,464 |
| | | በጨረር የሚሰራ ቴርሞ ሜትር | 837 |
| | | ቴርሞካፕል ካሊብሬሽን | 3,348 |
| 2 | ከባቢ አየር ሙቀት እና ወበቅ መለኪያ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን | የቴርሞ-ሃይግሮሜትር ካሊብሬሽን አገልግሎት መስጠት | 4,464 |
| | | የከባቢ አየር አንጻራዊ እርጥበት መጠን መለኪያ (Hygrometer) ካሊብሬሽን አገልግሎት መስጠት | 2,232 |
| 3 | የክላይማቲክ ቻምበር ካሊብሬሽን አገልግሎት | የኦቨን ካሊብሬሽን አገልግሎት | 2,232 |
| | | የፈርነስ ካሊብሬሽን አገልግሎት | 2,232 |
| | | የኢንኩቤተር ካሊብሬሽን አገልግሎት | 2,232 |
| | | የማቀዝቀዣ ካሊብሬሽን አገልግሎት | 2,232 |
| | | የኮልድ ሩም ካሊብሬሽን አገልግሎት | 2,232 |
| 4 | የእህል/የጥራጥሬ እርጥበት ይዘት መለኪያ መሳሪያዎች ካልብሬሽን | የእህል/የጥራጥሬ እርጥበት ይዘት መለኪያ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን | 2,232 |
| | | የቡና እርጥበት ይዘት መለኪያ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን | 4,464 |
| 5 | . የኤሌክትሪክ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን አገልግሎት | የሪዚስታንስ መሊኪያ መሳሪያ ካሊብሬሽን | 2,940 |
| | | የታወቀ የሪዚስታነስ መጠን አመንጪ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን | 2,940 |
| | | ዲኬድ ሬዚስተር/ረዚስታንስ ብሪጅ ካልብሬሽን | 3,528 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ደብል ብሪጅ ካልብሬሽን | 4,704 |
| | | ኮንዳክቲቭ ሜትር ካልብሬሽን | 1,764 |
| | | ቮልት ሜትር ካሊብሬሽን | 2,900 |
| | | ዲሲ ቮልት ሜትር 1.018 V እና 10 V ካልብሬሽን | 2,352 |
| | | የኢንሱሌሽን ቴስተር ካልብሬሽን | 2,352 |
| | | ሚሊ አምፒር ካሊብሬተር ካልብሬሽን | 4,704 |
| | | ክላምፕ ሜትር ካልብሬሽን | 2,352 |
| | | ፓወር ሰፕላይ/ፓወር ሜትር ካልብሬሽን | 4,704 |
| | | ትራንስፎርመር/ኢነርጂ ሜትር ካልብሬሽን | 2,352 |
| | | ጀነሬተር ቴስተር ካልብሬሽን | 3,528 |
| | | መልቲ ሜትር ካልብሬሽን | 7,056 |
| | | መልቲ ፈንክሽናል ካልብሬተር ካልብሬሽን | 3,528 |
| 6 | የጊዜና ድግግሞሽ መለኪያ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን አገልግሎት | ታኮሜትር (በጨረር የሚሰራ) ካልብሬሽን | 1,176 |
| | | ፍሪኩዌንሲ ጀነሬተር ካልብሬሽን | 1,764 |
| | | ፍሪኩዌንሲ ካውንተር ካልብሬሽን (10 ካልብሬሽን ማነጻጸሪያ ነጥብ) | 2,352 |
| | | ሴንትሪፉጅ ካልብሬሽን | 2,352 |
| | | መቆጣጠሪያ (ስቶፕዎች)/ታይመር ካልብሬሽን | 1,176 |
| 7 | የፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ ባህሪያት ካልብሬሽን አገልግሎት | ዌቭሌንግዝ፣ አብሰዞርባንስ፣ ትራንስሚታንስ፣ ስፔክተራል ሪፈረንስ | 3,145 |
| | | የቀለም ባህሪ ልኬት አወሳሰን አገልግሎት | 1,887 |
| | | ከለር ረንደሪን ኢንዴክስ የብርሃን ምንጭ | 1,258 |

**የመካኒካል ሥነ-ልክ መሪ ሥራ አስፈፃሚ የሚሰጡ አገልግሎቶች**

| ተ.ቁ | አገልግሎት | የአገልግሎቱ አይነት | የአገልግሎቱ ክፍያ ዋጋ(በብር) |
|---|---|---|---|
| 1 | የይዘት መለኪያ መሣሪያዎች ካሊብሬሽን አገልግሎት | ቡሬት | 1,097 |
| | | ፍላስክ | 439 |
| | | የባለብዙ ደሊቨሪ ዲስፔንሰር | 5,270 |
| | | ፓይፔት/ሲሊንደር ካሊብሬሽን | 878 |
| | | የፕሩቨር ካሊብሬሽን | 2,635 |
| | | የነዳጅ እና ሌሎች ፈሳሽ ቆጣሪዎች ካሊብሬሽን | 4,391 |
| | | የነዳጅ ማራገፊያና መጫኛ ቆጣሪ | 7,026 |
| 2 | የታንከር መለኪያ መሳሪያዎች ካልብሬሽን አገልግሎት | ፈሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር እስከ 5,000 ሊትር | 3,291 |
| | | ፈሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር እስከ 10,000 ሊትር | 8,227 |
| | | ፈሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር እስከ 30,000 ሊትር | 16,453 |
| | | ፈሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር እስከ 50,000 ሊትር | 24,680 |
| | | ፈሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር እስከ 70,000 ሊትር | 28,793 |
| | | ፈሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር እስከ 100,000 ሊትር | 37,020 |
| 3 | የእፍግታ (ዴንስቲ) መለኪያ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን አገልግሎት | የእፍግታ (ዴንስቲ) | 878 |
| 4 | የሚዛን መለኪያ መሳሪያዎች ካልብሬሽን አገለግሎት | ኤሌክትሮኒክ ሚዛን (እስከ 60 ኪግ ) 10 ማነጻጸሪያ ነጥብ | 878 |
| | | ሚዛን (እስከ 300 ኪግ) 10 ማነጻጸሪያ ነጥብ | 1,317 |
| | | ሚዛን (እስከ 1000 ኪግ) 10 ማነጻጸሪያ ነጥብ | 1,757 |
| | | የአስፋልት/የኮንክሪት ሚዛን በቋት አስከ 200 ኪግ | 2,635 |
| | | የአስፋልት/የኮንክሪት ሚዛን በቋት አስከ 500 ኪግ | 3,513 |
| | | የአስፋልት/የኮንክሪት ሚዛን በቋት አስከ 1000 ኪግ | 5,270 |
| | | የአስፋልት/የኮንክሪት ሚዛን በቋት አስከ 2000 ኪግ | 6,148 |

| ተ.ቁ | አገልግሎት | የአገልግሎቱ አይነት | የአገልግሎቱ ክፍያ ዋጋ(በብር) |
|---|---|---|---|
| | | ማሽን ተንጠልጣይ/ተገጣሚ ሚዛን እስከ 2000 ኪግ | 3,513 |
| 4 | የግዝፈት ማነጻጸሪያ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን አገልግሎት | የክብደት ማነጻጸሪያ ክላስ OIML E2 | 2,635 |
| | | የክብደት ማነጻጸሪያ ክላስ OIML F1/F2 | 1,757 |
| | | የክብደት ማነጻጸሪያ ክላስ OIML M | 823 |
| | | የክብደት ማነጻጸሪያ ክላስ OIML M, 20 ኪ.ግራም | 439 |
| | | የክብደት ማነጻጸሪያ ክላስ OIML M, 50 ኪ.ግራም | 1,098 |
| | | የክብደት ማነጻጸሪያ ክላስ OIML M, 100 ኪ.ግራም | 4,391 |
| | | የግዝፈት መጠነ ልኬት እስከ 20 ኪ.ግራም በነጠላ | 1,098 |
| 5 | የኃይል መለኪያ መሳሪያዎች ካልብሬሽን አገልግሎት | ፎረስ ትራንስዱሰር | 9,679 |
| | | ዩንቨርሳል እስትሬግዝ መፈተሻ ማሽን | 6,675 |
| | | የቴንሳይል እስትሬንግዝ ጥንካሬ መፈተሻ ማሽን | 5,340 |
| | | የኮንክሪት/ብሎኬት ጥንካሬ መፈተሻ መሳሪያ | 5,340 |
| | | የአፈር/የአስፋልት ጥንካሬ መፈተሻ ማሽን እስከ 100 kN | 4,005 |
| 6 | የሀርድነስ መፈተሻ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን አገልግሎት | ሃርድነስ ብሎክ 0-300 Kgf | 2,670 |
| | | ሃርድነስ ቴስቲንግ ማሽን ፣0-70 HRC | 3,338 |
| | የቶርክ መፈተሻ መሳሪያዎች ካልብሬሽን አገልግሎት | ቶርክ ረንች ትራንስዱሰር | 5,340 |
| | | ቶርክ ረንች ቴስተር | 5,117 |
| 7 | የግፊት መለኪያ መሳሪያዎችካሊብሬሽን | ፕሬዡር ባላንስ | 21,360 |
| | | ዲፈረንሻል የግፊት ጌጅ መለኪያ መሳሪያ | 10,680 |
| | | የግፊት መለኪያ ጌጆች/አመልካቾች | 5,340 |
| | | የግፊት መለኪያ ጌጅ ለክላስ A እና B | 2,003 |
| | | የግፊት መለኪያ ጌጅ ለክላስ C | 1,335 |
| | | ባሮሜትር መለኪያ መሳሪያ | 5,340 |
| | | የደም ግፊት መለኪያ መሳሪያ | 668 |

| ተ.ቁ | አገልግሎት | የአገልግሎቱ አይነት | የአገልግሎቱ ክፍያ ዋጋ(በብር) |
|---|---|---|---|
| 8 | የዳይሜንሽን መለኪያ መሳሪያዎች ካልብሬሽን አገልግሎት | ጌጅ ብሎክ ግሬድ 0 እስከ 100 ሚ.ሜ (በነጠላ ቁጥር) | 429 |
| | | ጌጅ ብሎክ ግሬድ 1 እስከ 100 ሚ.ሜ (በነጠላ ቁጥር) | 257 |
| | | ጌጅ ብሎክ ግሬድ 2 እስከ 100 ሚ.ሜ (በነጠላ ቁጥር) | 215 |
| | | ማስመሪያ እስከ 2 ሜትር | 858 |
| | | ተጠቅላይ ሜትር እስከ 50 ሜትር | 1,030 |
| | | ድስፔንሰር አስከ 3 ሜትር | 858 |
| | | ካሊፐር 0-150 ሚሜ | 1,073 |
| | | ካሊፐር/ሄይት ጌጅ/ማክሮሜትር ከ-150 ሚሜ | 1,287 |
| | | ዲያል ኢንዲከተር 0 - 100 ሜሜ | 1,716 |
| | | ፊለር ጌጅ/ ፔንትሮ ሜትር/ ጎኖሳ/ቲክነስ ጌጅ | 858 |
| | | ወንፊት መለኪያ | 1,716 |
| 9 | የቅየሳ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን አገልግሎት | ቶታል ስቴሽን | 20,597 |
| | | ቴዶላይት | 6,866 |
| | | ሌቭለር | 3,433 |
| 10 | የድምጽና እርግብግቦሽ መሳሪያዎች ካልብሬሽን አገልግሎት | ማይክሮፎን | 987 |
| | | የፍጥነት መለኪያ | 823 |
| | | የድምፅ ደረጃ ሜትር | 823 |

## የኬሚካል ሥነ-ልክ ምርምር መሪ ሥራ አስፈፃሚ

| ተ.ቁ | አገልግሎት | የአገልግሎቱ አይነት | የአገልግሎቱ ክፍያ ዋጋ(በብር) |
|---|---|---|---|
| 1 | የማመሳከሪያ ስረቶች አቅርቦት | 10,000 ብር በናሙና | |
| | የላብራቶሪ ብቃት ንፀፅር ናሙና ስረቶች አቅርቦት አገልግሎት | 10,000 ብር በናሙና | |

## የህክምና መሳሪያዎች መሪ ስራ አስፈጻሚ

### የሃይቴክ መሳሪያዎች ጥገና አገለግሎት

| ተ.ቁ | አገልግሎት | የአገልግሎቱ አይነት | የአገልግሎቱ ክፍያ ዋጋ(በብር) |
|---|---|---|---|
| 1 | የባዮሜዲካል መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | ዉስብስብ የሆኑ የባዮሜዲካል መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 25,865 |
| | | ዉስብስብነታቸዉ መከካለኛ የሆኑ የባዮሜዲካል መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 12,933 |
| | | ዉስብስብነታቸዉዝቅተኛ የሆኑ የባዮሜዲካል መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 6,466 |
| 2 | የሜዲካል ኢሜጂንግ መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | ዉስብስ የሆኑ የሜዲካል ኢሜጂንግ መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 34,487 |
| | | ዉስብስብነታቸዉ መከካለኛ የሆኑ የሜዲካል ኢሜጂንግ መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 17,243 |
| | | ዉስብስብነታቸዉ ዝቅተኛ የሆኑ የሜዲካል ኢሜጂንግ መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 8,622 |
| 3 | የክሊኒካል ላቦራቶሪ መሣሪያዎች ጥገና | ዉስብስ የሆኑ የክሊኒካል ላቦራቶሪ መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 21,211 |

| ተ.ቁ | አገልግሎት | የአገልግሎቱ አይነት | የአገልግሎቱ ክፍያ ዋጋ(በብር) |
|---|---|---|---|
| | **አገልግሎት** | ዉስብስብነታቸዉ መከካለኛ የሆኑ የክሊኒካል ላቦራቶሪ መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 10,605 |
| | | ዉስብስብነታቸዉዝቅተኛ የሆኑ የክሊኒካል ላቦራቶሪ መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 5,303 |
| | | ዉስብስ የሆኑ የክሊኒካል ላቦራቶሪ መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 21,211 |
| 4 | የአናሊቲካል መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | ዉስብስብ የሆኑ የአናሊቲካልመሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 21,111 |
| | | ዉስብስብነታቸዉ መከካለኛ የአናሊቲካል መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 10,556 |
| | | ዉስብስብነታቸዉ ዝቅተኛ የሆኑ የአናሊቲካል መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 5,278 |
| 5 | የራዴሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ጥገና እና ካሊብሬሽን አገልግሎት | ዉስብስብ የሆኑ የኑኩለር መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 38,150 |
| | | ዉስብስብነታቸዉ መከካለኛ የኑኩለር መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 22,890 |
| | | ዉስብስብነታቸዉ ዝቅተኛ የሆኑ የኑኩለር መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 7,630 |
| | | ቴርሞ ሉሚነሰንት ዶዚሜትር | 241 |
| | | ኦፕቲካል ስቲሙሌትድ ሉሚነሰንስ | 1,203 |
| | | መልቲመትር ዶዞሜትሪ ሲሰተም | 1805 |
| | | ቻምበር | 1,203 |
| | | ሰርቬይ ሜትር | 902 |
| | | ኤሌክትሮኒክ ፖኬት ዶዞሜትር | 902 |
| | | ምትክ ካልብሬሽን ሰርተፍኬት መስጠት | 230 |
| 6 | **የልኬትና ፍተሻ መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት** | ዉስብስብ የሆኑ የልኬትና ፍተሻ መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 30,691 |
| | | ዉስብስብነታቸዉ መከካለኛ የሆኑ የልኬትና ፍተሻ መሣሪያዎች ጥገና አገልግሎት | 11,509 |
| | | ዉስብስብነታቸዉ ዝቅተኛ የሆኑ የልኬትና ፍተሻ መሣሪያዎች ጥገና | 7,673 |

| ተ.ቁ | አገልግሎት | የአገልግሎቱ አይነት | የአገልግሎቱ ክፍያ ዋጋ(በብር) |
|---|---|---|---|
| | | አገልግሎት | |

## የስልጠናና ማማከር አገልግሎት

| | የአገልግሎቱ አይነት | | አገልግሎቱን የሚሰጥ አካል | ዋጋ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የስልጠናና ማማከር አገልግሎት | የሞጁላር ስልጠና አገልግሎት በሠው/በቀን | ➢ የኤሌክትሮ ማግኔቲክ እና ሙቀት ሥነ-ልክ መሪ ሥራ አስፈፃሚ<br>➢ የመካኒካል ሥነ-ልክ መሪ ሥራ አስፈፃሚ<br>➢ የኬሚካል ሥነ-ልክ ምርምር መሪ ሥራ አስፈፃሚ<br>➢ የሕክምና መሣሪያዎች መሪ ሥራ አስፈፃሚ<br>➢ የአናልቲካል ፣ ልኬትና ፍተሻ እና ራዲዬሽን መሪ ስራ አስፈጻሚ | 1,736 |
| | | የተገልጋይ ዲላማ ተኮር ስልጠና አገልግሎት | | 1,970 ብር በሰዉ/በቀን |
| 2 | የሥራ ላይ የልምምድ-ትስስር ስልጠና አገልግሎት | የስራ ላይ የልምምድ-ትስስር ስልጠና በሰው/በቀን<br><br>ከ5 ቀናት እስከ አንድ ወር | | 3,940 |
| 3 | | የአደረጃጀት ማማከር አገለግሎት በሰው/በቀን<br><br>ከ አንድ ቀን እስከ አምስት ወራት | | 1,970 |
| 4 | የአገልግሎቶች መረጣና አጠቃቀም ውጤታማነት ማማከር አገልግሎት | የአገልግሎቶች መረጣና አጠቃቀም ውጤታማነት ማማከር አገልግሎት በሰው/በቀን | | 1,970 |

## የሃይቴክ መሳሪያዎች ተከላ እና ኮምሽኒግ ማማከር አገልግሎት

| | የአገልግሎቱ አይነት | አገልግሎቱን የሚሰጥ አካል | አይነት | ዋጋ |
|---|---|---|---|---|
| | የሃይቴክ መሳሪያዎች ተከላ እና ኮምሽኒግ ማማከር አገልግሎት | አናልቲካል ፣ ልኬትና ፍተሻ እና ራዲዬሽን መሪ ስራ አስፈጻሚ<br><br>ከ1 ቀን እስከ አምስት ቀናት | የሃይቴክ መሳሪያዎች ተከላ እና ኮምሽኒግ ማማከር አገልግሎት በሠው/በቀን | 9,850 |
| | የሃይቴክ መሳሪዎች አገኛኘት ማማከር አገልግሎት | | የቴክኖሎጂ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አገልግሎት በቀን | 1,522 |
| | | | የመሳሪያዎች ግዢ ቴክኒካዊ መስፈርት ዝግጅት አገልግሎት በቀን | 1,522 |
| | | | ብቁ ተወዳዳሪ የቴክኖሎጂ አቅራቢዎችን የመምረጥ አገልግሎት በቀን | 1,903 |
| | | | በግዢ የቀረቡ መሳሪያዎች ቴክኒካዊ ኢንስፔክሽን አገልግሎት በቀን | 1,142 |

# 4. ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች

የኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቁና ተዓማኒ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ ተቋሙ የሚመራባቸው ጥብቅ የአገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲዎች፣ መርሆችና ደንቦች አሉት። እነዚህ ፖሊሲዎች ተቋሙ ከደንበኞቹና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያጠናክሩ ናቸው።እነዚህ ፖሊሲዎች ተቋሙ በባለድርሻ አካላትና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዘንድ ተአማኒነት እንዲኖረው ያደርጉታል።

### i. የጥራት ፖሊሲ

የኢንስቲትዩቱ ዋነኛ መመሪያ ISO/IEC 17025 የተሰኘው ዓለም አቀፍ የላቦራቶሪዎች ብቃት መመዘኛ ስታንዳርድ ሲሆን ዋና አላማውም በላቦራቶሪ የሚሰጡ የልኬትና የካሊብሬሽን ውጤቶች ፍጹም ትክክለኛና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ። በተጨማሪም ፖሊሲው፣ ማንኛውም አገልግሎት የሚሰጠው በሰለጠነ ባለሙያ፣ በጸደቀ የአሰራር ዘዴ (Validated Method) እና ደረጃውን በጠበቀ መሣሪያ ብቻ እንደሆነ አቅጣጫ አስቀምጧል።

ii. **የገለልተኝነትና የፍትሃዊነት ፖሊሲ**

- ተቋሙ አገልግሎት ሲሰጥ ከማንኛውም ወገንተኛነት የጸዳ መሆን ስለሚኖርበት እና በተገልገዮቹ ዘንድ ተዓማኒ እንዲሆን ለማስቻል አገልግሎቱ በማንኛውም የንግድ፣ የፋይናንስ ወይም የፖለቲካ ተጽዕኖ ስር አለመሆኑን ያመላክታል።
- ለሁሉም ደንበኞች (መንግስታዊም ሆኑ የግል) እኩልና ፍትሃዊ አገልግሎት መስጠት።
- የውሳኔ አሰጣጡም በሳይንሳዊ መረጃ ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው።

iii. **የምስጢራዊነት ፖሊሲ**

- የደንበኞች መረጃና የንግድ ሚስጥር መጠበቅ የተቋሙ ቀዳሚ ግዴታ ነው።
- ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የሚገኙ የደንበኞች የቴክኒክ መረጃዎች፣ የምርት ውጤቶችና የፈጠራ ስራዎች ያለ ደንበኛው ፈቃድ ለሦስተኛ ወገን ተላልፈው አይሰጡም።
- **ልዩ ሁኔታ፡** መረጃው ለህግ አካል እንዲሰጥ በመንግስት ካልታዘዘ በስተቀር፣ ተቋሙ በምስጢር የመጠበቅ የሙያ ግዴታ አለበት።

iv. **የልኬት ተከታታይነት ፖሊሲ**

- ይህ ፖሊሲ የኢንስቲትዩቱ የቴክኒክ ህልውና መሠረት ሲሆን በኢትዮጵያ የሚሰጥ ማንኛውም የልኬት ውጤት ወደ ዓለም አቀፉ የልኬት ስርዓት ያልተቋረጠ ሰንሰለት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፣
- ተቋሙ የሚጠቀማቸው የመጀመሪያ ደረጃ የመለኪያ ማነፃፀሪያ መሳሪያች በየጊዜው በዓለም አቀፍ ተቋማት (እንደ BIPM ወይም PTB) መረጋገጥ አለባቸው።

v. **የደንበኞች እርካታና የቅሬታ አፈታት ፖሊሲ**

- ተገልጋዮች ለአገልግሎቱ ዋጋ የሚሰጡበትን ስርአት ዘርግቶ እየሰራ ይገኛል፣
- ተቋሙ በየጊዜው የደንበኞችን አስተያየት በመሰብሰብ አገልግሎቱን የማሻሻል ግዴታ አለበት፣
- አንድ ደንበኛ በአገልግሎቱ ካልረካ ቅሬታውን የሚያቀርብበትና በገለልተኛ አካል ተመርምሮ ምላሽ የሚያገኝበት ግልጽ አሰራር ተዘርግቷል፣ (አባሪ የተደረገውን የቅሬታ አቀራረብ ስነስረዓት ይመልከቱ)

vi. **የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ**

ይህ ደንብ አገልግሎቱ በምን ያህል ጊዜና ጥራት መጠናቀቅ እንዳለበት ይወስናል በዚህም ለእያንዳንዱ አገልግሎት (ለምሳሌ የክብደት ካሊብሬሽን) የሚፈጀው ጊዜና የሚከፈለው ክፍያ በግልጽ ታውቆ ለደንበኛው እንዲታወቅ ይደረጋል፣

ኢንስቲትዩቱም አላስፈላጊ ቢሮክራሲን በማስቀረት አገልግሎቱን በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ አገልግሎቱን ይሰጣል፣

## 5. ውጫዊ ግንኙነት እና አጋርነት

የኢንስቲትዩቱ ባለድርሻ አካላት በተቋም ስራና ውጤት ላይ ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ተሳትፎ ወይም ፍላጎት ያላቸውን ቡድኖች ያካትታል። እነዚህ አካላት በተቋሙ ስኬት ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም በውድቀቱ ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል። በተመሳሳይ መልኩ፣ የእነሱ ድርጊትና አቋም በኢንስቲትዩቱ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የራሱ የሆነ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ የማሳረፍ አቅም አለው። የኢንስቲትዩቱ አገልግሎቶች ተገልጋዮች ማለት የተቋሙን አገልግሎት የሚጠቀሙ ወይም በእሴቱ ላይ ጥገኝነት ያላቸው አካላትን ይጨምራል። በባለድርሻ አካላት ዝርዝር ውስጥ ተገልጋዮች የውጭ ባለድርሻ አካላት ተብለው የሚመደቡ ቢሆንም፣ ለኢ.ስ.ኢ ህልውና ግን የጀርባ አጥንት ናቸው።

### 5.1. የኢንስቲትዩቱ ተገልጋዮች እና ባለድርሻ አካላት

**ተገልጋዮች**

- አምራችና አገልግሎት ሰጪ ኢንዱስትሪዎች
- የሳይንስ መሳሪያዎች ተጠቃሚና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት
- የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
- የጥናትና ምርምር ተቋማት
- የጥራት ተቆጣጣሪ አካላት፡
    - ሕጋዊ ሥነ-ልክ
    - የምግብ መድሐኒትና የጤና ክብካቤ ባለሥልጣን
    - የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን
    - አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
    - የኢነርጂ ባለስልጣን
    - የቴሌኮሚኒኬሽን ባለስልጣን
    - የጤና ጥበቃ ተቋማት
    - የሙያ ማሕበራት

**ባለድርሻ አካላት**

- ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
- ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- ጤናሚኒስቴር
- የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት
- የሚኒስትሮች ም/ቤት
- የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት
- የገንዘብ ሚኒስቴር
- ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
- ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

Table 1: **የተገልጋዮች ዝርዝር መግለጫ እና ትንተና**

| ተ.ቁ | ተገልጋዮች | ኢንስቲትዩቱ ከተገልጋዮች የሚፈልጋቸው ባህርያት | ተገልጋዮች ከኢንስቲትዩቱ የሚፈልጉት (ምርት/አገልግሎት) | ተገልጋዮች በኢንስቲትዩቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች | የተገልጋዮች የተጽዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ፤ መካከለኛ፤ ዝቅተኛ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አምራችና አገልግሎት ሰጪ ኢንዱስትሪዎች | • ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የልኬት መሳሪያዎችን መጠቀም<br>• አለም አቀፍ አሀዶችን ጥቅም ላይ ማዋል<br>• የካሊብሬሽን ሰርተፍኬቶች በአግባቡ ተጠቃሚነትን | • የካሊብሬሽንና የጥገና አገልግሎት<br>• በሥነ-ልክ ዘርፍ ምክርና ስልጠና | • ኢንዱስትሪዎች የሚጠቀሙባቸውን ሚዛኖችና መለኪያዎችን በወቅቱ ለምርመራና ለካሊብሬሽን ካላቀረቡ<br>• ለጥራት ትኩረት አለመስጠት | ከፍተኛ |
| 2 | የሳይንስ መሳሪያዎች ተጠቃሚና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት | • ትክክለኛና ዉጤታማ የሳይንስ መ/አጠቃቀም<br>• የሳይንስ መሳሪያዎች ስራ አመራር እና አደረጃጀት<br>• ተባባሪነትና ምላሽ ሰጪነት | • የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት<br>• በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ምክር፣ ስልጠና እና የመረጃ አገልግሎት<br>• የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት | ● መሣሪያዎች ያለ ቅድመ ምክክር ወደ ሀገር ካስገቡ | ከፍተኛ |
| 3 | የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | • በከፍተኛ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የሥነ-ልክ ኮርሶች ተካተዉ እንዲሰጡ<br>• በሥነ-ልክና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ተማሪዎች ተግባራዊ ምርምር እንዲያደርጉ<br>• በሥነ-ልክና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ የዳበረ ክህሎት ያላቸዉ ተመራቂዎች<br>• በሳይንስ መሳሪያዎች አዳዲስ የምህንድስና ዘርፍ ትምህርት እንዲጀመር | • ምክር፣ ስልጠና፣ ጥገናና የካሊብሬሽን አገልግሎቶች<br>• ለምርምር መሥሪያ የላቦራቶሮች ድጋፍ<br>• የኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ድጋፍ<br>• የካሪኩለም ዝግጅት ድጋፍ | • በተግባር የተደገፈ ትምህርትና ስልጠና ከሌለ<br>• በቂ የምርምር ሥራዎች ድጋፍ ካልተደረጉ<br>• በክህሎትና ጽንሰ ሀሳብ የዳበረ ተመራቂዎች ማፍራት ካልተቻለ | ከፍተኛ |
| 4 | የጥናትና ምርምር ተቋማት | • ትክክለኛነቱ የተረጋጠ የልኬት መሳሪያዎችን መጠቀም<br>• አለም አቀፍ አሀዶችን ጥቅም ላይ ማዋል<br>• የጥናትና ምርምር ስራዎችን በትብብር መስራት | • የካሊብሬሽንና የጥገና አገልግሎት<br>• ምክርና ስልጠና<br>• ለምርምር መሥሪያ የላቦራቶሪዎች ድጋፍ | • የምርምር ተቋማት የሚጠቀሙባቸውን መሣሪያዎች በኢንስቲትዩቱ ሳያረጋግጡ ጥናት ካካሄዱ<br>• በቂ የምርምር ሥራዎች ድጋፍ ካልተከናወኑ | ከፍተኛ |

| ተ.ቁ | ተገልጋዮች | ኢንስቲትዩቱ ከተገልጋዮች የሚፈልጋቸው ባህርያት | ተገልጋዮች ከኢንስቲትዩቱ የሚፈልጉት (ምርት/አገልግሎት) | ተገልጋዮች በኢንስቲትዩቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች | የተገልጋዮች የተጽዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ፤ መካከለኛ፤ ዝቅተኛ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | የጥራት ተቆጣጣሪ አካላት | • ቅንጅታዊ አሰራር እንዲፈጥሩ<br>• ተቋማትን ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ መሳሪያዎች እንዲጠቀሙ የመቆጣጠርና የማስፈጸም ብቃት | • ምክርና ስልጠና<br>• የካሊብሬሽንና የጥገና አገልግሎት<br>• ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት | • ተቆጣጣሪ አካላት የቴክኒክ ውሳኔዎቻቸውን በኢንስቲትዩቱ ሳይንሳዊ ልኬት ላይ ካልመሰረቱ | ከፍተኛ |
| 6 | የጤና ጥበቃ ተቋማት | ትክክለኛነቱ የተረጋጠ የህክምና መሳሪያዎችን መጠቀም<br><br>የህክምና መሳሪያዎች ስራ አመራርና አደረጃጀት እንዲኖር | ምክርና ስልጠና<br><br>የካሊብሬሽንና የጥገና አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት | • የላቦራቶሪ መሣሪያዎቻቸውን በወቅቱ ካላስመረመሩ<br>• ለደህንነት ስታንዳርዶች ትኩረት አለመስጠት | ከፍተኛ |

Table 2: ባለድርሻ አካላት ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት | ኢንስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው ባህርያት | ባለድርሻ አካላት ከኢንስቲትዩቱ የሚፈልጉት (ምርት/አገልግሎት) | ባለድርሻ አካላት በኢንስቲትዩቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች | የባለድርሻ አካላት የተፅዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ፣መካከለኛ፣ ዝቅተኛ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር | ➢ የአመራርና የቴክኒክ ድጋፍ | ➢ ውጤታማና ቀልጣፋ አፈጻጸም | ➢ የዘገዩ ቴክኒካዊ ውሳኔዎች<br>➢ በምርቶች ኤክስፖርት ላይ ትክክለኛ የልኬት ስታንዳርድን እንዲተገበር ካላበረታታ | **ከፍተኛ** |
| 2 | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ➢ ከአምራች ኢንዱስትሪው ጋር ተቀራርበን የምንሰራበትን መንግድ ማመቻቸት | ➢ ውጤታማና ቀልጣፋ አፈጻጸም | ➢ አምራቾች የልኬት ስታንዳርድን እንዲከተሉ ግፊት ካላደረገ | **ከፍተኛ** |
| 3 | የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት | ➢ ወቅታዊና ቀጣይነት ያለው የክትትልና ድጋፍ<br>➢ የቅንጅታዊ አሰራር ድጋፍ | ➢ ወቅቱን የጠበቀ ዕቅድና ሪፖርት | ➢ ተቋሙ የሚመራበት ጠንካራና ዘመናዊ የህግ ማዕቀፍ በፍጥነት ካልጸደቀ ወይም የቁጥጥር ስልጣኑ ውስን ከሆነ | መካከለኛ |
| 4 | የሚኒስትሮች ም/ቤት | ➢ የደንብ ማሻሻያ ማጽደቅ | ➢ የተልዕኮ አፈጻጸም | ➢ በሚኒስትሮች ደረጃ ለስነ-ልክ ዘርፍ የሚሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ ከሆነ | ከፍተኛ |
| 5 | የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት | ➢ የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሠራር | ➢ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የአለካክ ስርዓት<br>➢ የካሊብሬሽን አገልግሎት<br>➢ ተጠናከረ ቅንጅታዊ አሠራር | ➢ የጥራት ቁጥጥር ስርአቱ በሳይንሳዊ ልኬት ላይ ያልተመሰረተ ከሆነ | መካከለኛ |
| 6 | ገንዘብ ሚኒስቴር | ➢ በቂ ካፒታል እና መደበኛ በጀት | ➢ ተዘጋጅቶ የቀረበ የፕሮግራም በጀት ዕቅድ<br>➢ ህጋዊና ውጤታማ የፋይናንስ አፈጻጸም | ➢ ለላቦራቶሪ ዕቃዎች ግዢ እና ለጥገና የሚሆን በቂ በጀት ካልፈቀደ ወይም የውጭ ምንዛሬ እጥረት ካጋጠመ | ከፍተኛ |
| 7 | ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ | ➢ ቅንጅታዊ አሰራር፣ የምርምር | ➢ በአለካክ ላይ ቴክኒካዊ | ➢ የዲጂታልና የላቁ የልኬት | **መካከለኛ** |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት | ኢንስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው ባህርያት | ባለድርሻ አካላት ከኢንስቲትዩቱ የሚፈልጉት (ምርት/አገልግሎት) | ባለድርሻ አካላት በኢንስቲትዩቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች | የባለድርሻ አካላት የተፅዕኖ ደረጃ (ከፍተኛ፣መካከለኛ፣ ዝቅተኛ) |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሚኒስቴር | ፣ ቴክኒክና ፋይናንስ ድጋፍ | ድጋፍ | ቴክኖሎጂዎችን ከሀገሪቱ የሳይንስ ፖሊሲ ጋር ካላጣጣመ | |
| 8 | ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | ➢ የሰውሀብት አስተዳደርና የአደረጃጀት ድጋፍ | ➢ አግባብ ያለው የመንግስት ሰራተኛ አስተዳደር ህግ አፈጻጸም | ➢ ለዘርፉ የሚመጥን የተለየ የደመወዝ ስኬልና ጥቅማጥቅም ካልፈቀደ | ከፍተኛ |
| 9 | የክልላዊ መንግሥታት አስፈጻሚ መ/ቤቶች | ➢ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲፈጥሩ<br>➢ ተቋማትን ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ መሳሪያዎች እንዲጠቀሙ<br>➢ የመቆጣጠርና የማስፈጸም ብቃት | ➢ ምክርና ስልጠና<br>➢ የካሊብሬሽንና የጥገና አገልግሎት<br>➢ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት | ➢ የንግድና ገበያ ልማት ቢሮዎች ከኢንስቲትዩት ጋር በቅንጅት ካልሰሩ | ከፍተኛ |
| 10 | የሙያ ማህበራት | ➢ የሥነልክና የሳይንስ መሳሪያዎች ጉዳዮችን ማስተዋወቅና ማስተማር | ➢ ምክርና ስልጠና ፣ ፋይናንስና የተለያዩ ፋሲሊቲዎች | ➢ መንግስት ለዘርፉ ትኩረት እንዲሰጥ ግፊት ካላደረጉ ወይም ለባለሙያዎች መብት ካልቆሙ | ከፍተኛ |
| 11 | ሰራተኞች | ➢ ዕውቀት፣ልምድ፣ ክህሎትና ባህርይ ያለው | ➢ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና<br>➢ መልካም አስተዳደር<br>➢ መልካም የስራ አካባቢ<br>➢ የተሻለ ጥቅማጥቅም ደመወዝ | ➢ ውስጣዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩት ሰራተኞች የስራ ተነሳሽነት ካጡ ወይም የሙያ ስነ-ምግባር ጉድለት ካሳዩ | ከፍተኛ |
| 12 | ዋና ኦዲተር | ➢ ሙያዊ ድጋፍ | ➢ ህጋዊና ውጤታማ የመንግሥት ሀብትና ንብረት አጠቃቀምና አያያዝ | ➢ የተቋሙን የፋይናንስና የአፈጻጸም ክፍተት ብቻ ትኩረት ሰጥቶ የቴክኒክ ተግዳሮቶችን ግምት ውስጥ ካላስገባ | |

## 6. ደንበኞች መብትና ግዴታ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የደንበኛው ግዴታ | የኢንስቲትዩቱ ግዴታ |
|---|---|---|
| 1 | መሣሪያውን በንጽሕና ማቅረብ | የልኬት ምስጢራዊነትን መጠበቅ |
| 2 | የአገልግሎት ክፍያ በወቅቱ መክፈል | ትክክለኛና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው ውጤት መስጠት |
| 3 | የመሣሪያውን የቀድሞ ታሪክ (Manual) ማያያዝ | ለደንበኛው ሙያዊ ምክር መስጠት |

### 7. የኢንስቲትዩቱ የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ

ይህ ስትራቴጂ ተቋሙ የሚሰጣቸውን ሳይንሳዊ አገልግሎቶች፣ ያከናወናቸውን ተግባራት እና ያስመዘገባቸውን ውጤቶች ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ለጠቅላላው ህዝብ ተደራሽ የሚያደርግበት አካሄድ ነው። ተቋሙ የሥራ አፈፃፀሙን ለህዝብ በማሳወቅ ረገድ ግልጽነትን በማስፈን፣ ህዝቡ ተቋሙ ለሀገር ኢኮኖሚና ለዜጎች ደህንነት ምን እየሰራ እንደሆነ እንዲረዳ ያደርጋል።

ይህ ስትራቴጂ መረጃን መላክ ብቻ ሳይሆን ግብረ መልስ መቀበልንም ያካትታል። ተቋሙ አፈፃፀሙን ለህዝብ ሲያሳውቅ፣ ከህዝብ የሚመጡ ቅሬታዎችንና አስተያየቶችን የሚቀበልበት አሰራር ይዘረጋል። ይህ የሁለትዮሽ ግንኙነት ኢንስቲትዩቱ አገልግሎቱን እንዲያሻሽልና የተገልጋዮችን አመኔታ እንዲያተርፍ ይረዳዋል። በተለይም የጥራት ጉድለት በሚታይባቸው የንግድ መሣሪያዎች ላይ የሚሰሩ ስራዎችን ለህዝብ ይፋ ማድረጉ ህዝቡ ራሱን ከማጭበርበር እንዲከላከል ግንዛቤ ይፈጥራል።

## ለሕዝብ እና ለደንበኞች የሚደረግ ኮሙኒኬሽን

i. በየበጀት ዓመቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን የሚገልጽና በድረ-ገጽ የሚለቀቅ ሰነድ፣
ii. አዳዲስ ዓለም አቀፍ ዕውቅናዎች ሲገኙ ወይም አዳዲስ የላቦራቶሪ አገልግሎቶች ሲጀመሩ በጋዜጣ፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን መግለጫ መስጠት፣
iii. የኢንስቲትዩቱን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች፣ የተሳተፈባቸውን አውደ ጥናቶች እና ወቅታዊ መረጃዎችን በፌስቡክ፣ ቴሌግራም እና በይፋዊ ድረ-ገጹ ማጋራት።
iv. በየዓመቱ ግንቦት 12 (May 20) የሚከበረውን የዓለም የሜትሮሎጂ ቀን በመጠቀም፣ የልኬት ሳይንስ ለዕለት ተዕለት ሕይወትና ለንግድ ያለውን ፋይዳ ለሕዝብ ግንዛቤ መፍጠር፣
v. ከደንበኞች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በየጊዜው የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት የአገልግሎት ጥራትንና አፈጻጸምን መገምገም፣

### በተግባቦትና አህዘቦት ወቅትም

- የሚወጡ መረጃዎች ሁሉ በሳይንሳዊ መረጃ የተደገፉ ይሆናሉ፣
- ስኬቶችንም ሆነ ተግዳሮቶችን በግልጽ ማሳወቅ፣

- *መረጃዎች ለሰፊው ሕዝብ በቀላሉ በአማርኛ ቋንቋ ይቀርባሉ፣*

# 8. *ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚደረጉ ትብብሮች*

*የኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት በሀገሪቱ የጥራት መሠረተ ልማት ውስጥ እንደ መሠረት ይቆጠራል። ኢንስቲትዩቱ ከሌሎች የጥራት ተቋማት ጋር ያለው መስተጋብር እርስ በእርስ የተሳሰረና አንዱ ለሌላው ስኬት ወሳኝ የሆነ ሰንሰለት ነው።*

## 1. *ከኢትዮጵያ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ጋር ያለው መስተጋብር*

*የደረጃዎች ኢንስቲትዩት የምርቶችንና የአገልግሎቶችን ዝቅተኛ የጥራት መመዘኛ ያወጣል።*

- *የደረጃዎች ኢንስቲትዩት አዳዲስ ደረጃዎችን ሲያወጣ፣ በደረጃው ውስጥ የተጠቀሱት የልኬት እሴቶች (ለምሳሌ፡ የሙቀት መጠን፣ ክብደት፣ ርዝመት) በሳይንሳዊ መንገድ ሊለኩ የሚችሉ መሆናቸውን ከስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ጋር በመመካከር ያረጋግጣል።*
- *በደረጃዎች ዝግጅት ኮሚቴዎች ውስጥ የስነ-ልክ ባለሙያዎች በንቃት በመሳተፍ የልኬት ሳይንሱ በደረጃው ውስጥ በትክክል እንዲሰፍር ያደርጋሉ።*

## 2. *ከኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ያለው መስተጋብር*

*ተስማሚነት ምዘና ምርቶች የወጣላቸውን ደረጃ ማሟላታቸውን በላቦራቶሪ የሚመረምር ተቋም ነው።*

- *የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሚጠቀማቸው እጅግ ዘመናዊ የፍተሻ መሣሪያዎች ትክክለኛ ውጤት እንዲሰጡ፣ በየጊዜው በስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ካሊብሬት መደረግ አለባቸው። ያለ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ድጋፍ የተስማሚነት ምዘና ውጤቶች ተቀባይነት አይኖራቸውም።*
- *የምዘና ድርጅቱ የሚሰጠው የላቦራቶሪ ውጤት ከዓለም አቀፍ የልኬት ስርዓት ጋር የተገናኘ እንዲሆን ስነ-ልክ ኢንስቲትዩቱ እንደ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል።*

## 3. *ከኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ጋር ያለው መስተጋብር*

*አክሪዲቴሽን ማለት አንድ ላቦራቶሪ ወይም ተቋም በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቁ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ነው።*

- *አክሪዲቴሽን አገልግሎት ለአንድ ላቦራቶሪ ዕውቅና ከመስጠቱ በፊት፣ ያ ላቦራቶሪ የሚጠቀማቸው መሣሪያዎች በስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ካሊብሬት መደረጋቸውን እንደ ቅድመ-ሁኔታ ይጠይቃል።*
- *የአክሪዲቴሽን አገልግሎት ሌሎች ላቦራቶሪዎችን ሲገመግም የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ባለሙያዎችን እንደ ቴክኒክ ገምጋሚ ይጠቀማል።*

## 4. *ከህጋዊ ስነ-ልክ ተቆጣጣሪ ጋር ያለው መስተጋብር*

*ህጋዊ ስነ-ልክ (በአሁኑ ወቅት በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ስር የሚመራ) በገበያ ውስጥ ያሉ መለኪያዎችን ትክክለኛነት የመቆጣጠር ስልጣን አለው።*

- ተቆጣጣሪዎች በገበያ ላይ የሚጠቀሙባቸው የሥራ መመዘኛዎች (Working Standards) ትክክለኛነት በየጊዜው በስነ-ልክ ኢንስቲትዩት በሚደረግ የንፅፅር ስራ መረጋገጥ አለበት።
- ተቆጣጣሪዎች በልኬት ማጭበርበር ላይ እርምጃ ሲወስዱ፣ የቴክኒክ ክርክር ካጋጠማቸው የመጨረሻውን ሳይንሳዊ ውሳኔ የሚሰጠው ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ነው።

## 9. የማኀበረሰብ ተሳትፎ ተግባራት

የኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ከተቋቋመበት ዋና የቴክኒክ ተልዕኮ ባለፈ፣ እንደ አንድ የመንግስት ተቋም የማህበራዊ ኃላፊነትን መወጣት እንደ አንድ ስትራቴጂያዊ ተግባር ይወስደዋል።ተቋሙ ከሚሰጣቸው ሙያዊ አገልግሎቶች ባለፈ የሚከተሉትን ማኀበራዊ ኃላፊነቶች ይወጣል፣

### i. የትምህርትና የክህሎት ድጋፍ

ኢንስቲትዩቱ የነገ ሀገር ተረካቢ ተማሪዎች ስለ ሳይንስና ልኬት ያላቸው ግንዛቤ እንዲያድግ ያደርጋል።

- ለከፍተኛ ትምህርት ቤት እና ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የላቦራቶሪዎቹን ክፍት በማድረግ የተግባር ትምህርት እንዲያገኙ ያመቻቻል፣
- አቅም ለሌላቸው ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ (ደብተር፣ ቦርሳና እስክሪብቶ) ድጋፍ በማድረግ ማህበራዊ አጋርነቱን ያሳያል፣

### ii. የአካባቢ ጥበቃና የአረንጓዴ አሻራ

ተቋሙ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚጠራውን የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በንቃት ይሳተፋል።

- በየዓመቱ ሰራተኞቹን በማሳተፍ በተለያዩ አካባቢዎች ችግኞችን ይተክላል፣ የተተከሉትንም የመንከባከብ ስራ ይሰራል፣
- በላቦራቶሪዎቹ ውስጥ የሚወገዱ ኬሚካሎችና ቁሳቁሶች አካባቢን እንዳይበክሉ በከፍተኛ ጥንቃቄ በማስወገድ የማህበረሰቡን ጤና ይጠብቃል፣

### iii. ለችግረኛ ወገኖች የሚደረግ ድጋፍ

ኢንስቲትዩቱና ሰራተኞቹ በተለያዩ አጋጣሚዎች የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ያደርጋሉ፦

- በክረምት ወቅት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎችን ቤቶች በበጀትና በጉልበት የማደስ ስራ ይሰራል፣
- በበዓላት ወቅት ለተቸገሩ ወገኖች የቀለብና የማዕድ ማጋራት መርሃ ግብሮችን ያከናውናል፣
- የሰው ህይወት ለመታደግ የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች በየጊዜው የደም ልገሳ በማድረግ ማህበራዊ ግዴታቸውን ይወጣሉ፣

### iv. የሸማቾች መብትና ደህንነት ጥበቃ

- ህዝቡ በገበያ ውስጥ ሲገበያይ በሚዛንና በልኬት እንዳይበዘበዝ በየገበያውና በየመገናኛ ብዙኃኑ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ያከናውናል፣
- አነስተኛ የሀገር ውስጥ አምራቾች የልኬት ስርዓታቸውን እንዲያስተካክሉ ነፃ የሙያ ምክር መስጠት፣

### v. ሀገራዊ ጥሪዎችን መመለስ

ሀገሪቱ አስቸኳይ እርዳታ በሚያስፈልጋት ጊዜ (ለምሳሌ እንደ ኮቪድ-19 ያሉ ወረርሽኞች ወይም የተፈጥሮ አደጋዎች ሲከሰቱ) ተቋሙ የሚከተሉትን ያደርጋል፦

- ሰራተኞች ከደመወዛቸው ላይ በመቀነስ ለተለያዩ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች (ለምሳሌ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ) ድጋፍ ያደርጋሉ፣
- በጤና ተቋማት የሚገኙ የሙቀት መለኪያዎችንና ሌሎች የህክምና መሣሪያዎችን በነፃ በማረጋገጥ ወረርሽኞችን የመከላከል ስራ ውስጥ ይሳተፋል፣

## 10. ዓለም አቀፍ ወይም ቀጠናዊ አባልነቶች

